*ምናልባት ከኢሚግሬሽንና ስደተኞች ፌደራል ጽሕፈት ቤት የተላከልዎት/የተሰጠዎት ዉሳኔ፣ ይዞታው ከዚህ ኣገር ወደ መጡበት ኣገር እንዲባረሩ የሚያስጠነቅቅ ወይም እንዲባረሩ የሚያዝ ከሆነ፣ እባክዎን እዚህ ያለውን መረጃ እንዲከተሉ እናሳስብዎታለን:*

## በመቀመጫ ሕግ (የመኖሪያ ሕግ) መሰረት ጠቃሚ መልእክት

### በምዕራፍ 60a እዝባር 2d የመኖሪያ ሕግ መሰረት ማብራርያ

እርስዎን ወደ መጡበት ኣገር እንዳይባረሩ ሊያስከለክል በሚችል በሽታ የሚሰቃዩ ከሆነ፣ በዚህ በሽታ የሚሰቃዩ እንደሆነ የሚያረጋግጥ የሓኪም ማረጋገጫ ኣምጥተው ማሳመን ኣለብዎት። የእርስዎ ጉዳይ ለሚመለከተው የውጭ ኣገር ተወላጆች ጽሕፈት ቤት ይሄንን የሓኪም ማረጋገጫ ወዲያውኑ እንዲያቀርቡ ይገደዳሉ። „ወዲያውኑ" የሚለውን የጊዜ ገደብ ምልክት መጠበቅዎ ለማወቅ፣ የሓኪሙ ማረጋገጫ ላይ ተጽፎ ያለው ዕለት ነው ወሳኝነት ያለው። ይህ የሓኪም ማረጋገጫ፣ ከዚህ ኣገር መባረር ላቅመ ኣዳም ያልበቃ/ያልበቁ ልጅን/ልጆችን የሚጎዳ መሆኑን የሚያረጋግጥ ከሆነም፣ ይህንን ጽሑፍም ማቅረብ ኣለበዎት።
ይሄንን ሓኪም መርምሮ የጻፈውን የዉጤት ማረጋገጫ ሳያቀርቡ የቀሩ ከሆነ ወይም ዘግይተው ያቀረቡ ከሆነ፣ ከዚህ ኣገር የመባረር እርምጃ ሲወሰድ ማረጋገጫው ግምት ውስጥ ሊገባ ኣይችልም። እርስዎ ወይም ላቅመ ኣዳም ካልደረሱ ልጆችዎ ኣንዱ በበሽታ የሚሰቃዩ እንደሆናችሁ ብትገልጹም፣ የመባረር እርምጃ ሲወሰድ ተሰሚነት ኣይኖረውም። ማረጋገጫውን ወዲያውኑ ቢያቀርቡ እንኳን፣ ነገር ግን ይህ ያቀረቡት ማረጋገጫ ሕጉ የሚፈቅደውን የማያሟላ ሆኖ ከተገኘም፣ እንደዚሁ ተቀባይነት ኣይኖረውም።

የእርስዎ ጉዳይ የሚመለከተው የውጭ ኣገር ተወላጆች ጽሕፈት ቤት ባቀረቡት የሓኪም ማረጋገጫ ላይ በተጻፈው ጥርጣሬ ያደረበት ከሆነ፣ ባንድ ሓኪም ወይ ደግሞ በጽሕፈት ቤት ሓኪም ምርመራ እንዲደረግ ሊያዝ ይችላል። ይሄንን ትእዛዝ በቂ ባልሆነ ምክንያት ሳይከተሉ ከቀሩ፣ የሚመለከተው ጽሕፈት ቤት፣ የመባረር እርምጃ ሲወሰድ ያቀረቡትን ማረጋገጫ ግምት ውስጥ ላለማስገባት የሚያስችል መብት ኣለው።

### በምዕራፍ 50 እዝባር 4 የመኖሪያ ሕግ መሰረት ማብራርያ

በምዕራፍ 50 እዝባር 4 የመኖሪያ ሕግ መሰረት፣ ከዚህ ኣገር እንዲወጡ በሚገደዱበት ምክንያት፣ ማንኛውን ቤት መቀየር እንደዚሁም እርስዎ የሚኖሩበትን ከሚመለከተው የውጭ ኣገር ተወላጆች ጽሕፈት ቤት ወረዳ ከሶስት ቀናት በላይ ርቀው የሄዱ ከሆነ፣ ኣስቀድመው ለሚመለከተው የውጭ ኣገር ተወላጆች ጽሕፈት ቤት ማሳወቅ ኣለብዎት። ይሄንን ግዴታዎን ያፈረሱ ከሆነ፣ የመባረር እስር ቤት ውስጥ ሊገቡ የሚችሉ እንደሆኑ ማወቅ ኣለብዎት (ምዕራፍ 62 እዝባር 3 ቁጥር 2 የመኖሪያ ሕግ)።